# የፍትሕ መጓደልን የሚጠላ አምላክ

***መመሪያ፦*** ይህን መልመጃ ጸጥታ በሰፈነበት ቦታ ሆነህ ሥራ። ጥቅሶቹን ስታነብ በቦታው እንዳለህ አድርገህ አስብ። ሁኔታውን በዓይነ ሕሊናህ ለመሳል እንዲሁም በታሪኩ ውስጥ የተጠቀሱት ሰዎች ሲነጋገሩ ድምፃቸውን ለመስማትና ስሜታቸውን ለመረዳት ሞክር። ታሪኩ ሕያው እንዲሆንልህ አድርግ።

***ዋነኞቹ ባለታሪኮች፦*** አክዓብ፣ ኤልዛቤል፣ ናቡቴ እና ኤልያስ

***ታሪኩ በአጭሩ፦*** አክዓብ የወይን ተክል ቦታ ለማግኘት ሲል በኤልዛቤል ገፋፊነት ሰው አስገደለ።

## ❶ *ሁኔታውን ለማስተዋል ሞክር።—1 ነገሥት 21:1-26ን አንብብ።*

በዚህ ዘገባ ላይ የተገለጹት አራት ባለታሪኮች ምን ዓይነት መልክ ያላቸው ይመስልሃል?

አክዓብ__________

ኤልዛቤል__________

ናቡቴ__________

ኤልያስ__________

ከቁጥር 5-7 ባለው ዘገባ ላይ ኤልዛቤልና አክዓብ የተነጋገሩት በምን ዓይነት የድምፅ ቃና ይመስልሃል?__________

ቁጥር 13 ላይ ያለው ክንውን ሲፈጽም ምን ዓይነት ሁኔታ ሊኖር እንደሚችል ግለጽ።__________

ከቁጥር 20-26 ባለው ዘገባ ላይ ኤልያስና አክዓብ በምን ዓይነት የድምፅ ቃና የተነጋገሩ ይመስልሃል?__________

## ❷ *ጥልቅ ምርምር አድርግ።*

በቁጥር 7 እና 25 ላይ የተገለጹት የትኞቹ የኤልዛቤል መጥፎ ባሕርያት ናቸው?__________

በቁጥር 4 ላይ የተገለጹት የትኞቹ የአክዓብ መጥፎ ባሕርያት ናቸው?__________

አክዓብ የናቡቴን የወይን ተክል ቦታ ለመውሰድ ሲል እነማንን አስገድሏል? (2 ነገሥት 9:24-26ን አንብብ።)__________

አክዓብ በይሖዋ ዘንድ ምን ዓይነት ስም አትርፎ ነበር? (*ቁጥር 25ን እና 26ን በድጋሚ አንብብ።* በተጨማሪም 1 ነገሥት 16:30-33ን ተመልከት።)__________

❸ ***ከዚህ ታሪክ ያገኘሽውን ትምህርት ተግባራዊ አድርግ። ከዚህ በታች ስለሰፈሩት ሐሳቦች ምን ትምህርት እንዳገኘህ ጻፍ፦***

ይሖዋ ፍትሕ የጎደላቸው ድርጊቶችን የሚመለከት ስለመሆኑ ______________________________

______________________________

ይሖዋ ግፍ ለተፈጸመባቸው ሰዎች የሚያስብ ስለመሆኑ ______________________________

ይሖዋ የፍትሕ አምላክ መሆኑን ስላሳየበት መንገድ (ዘዳግም 32:4ን አንብብ።) ______________________________

______________________________

❹ ***ልትሠራበት የሚገባ ተጨማሪ ነገር፦***

ዛሬ ያሉ አንዳንድ ሰዎች የኤልዛቤል ዓይነት መንፈስ የሚያንጸባርቁት እንዴት ነው? (ራእይ 2:18-21ን አንብብ።) ______________________________

______________________________

የኤልያስ ዓይነት ድፍረት ማሳየት የሚያስፈልግህ ምን ዓይነት ሁኔታዎች ሲያጋጥሙህ ነው? ______________________________

______________________________

በአንተ ወይም በሌሎች ላይ የፍትሕ መጓደል ቢደርስ ስለምን ነገር እርግጠኛ መሆን ትችላለህ? ______________________________

______________________________

❺ ***ከዚህ ታሪክ ውስጥ ልብህን ይበልጥ የነካው ምንድን ነው? ለምንስ?***

______________________________

______________________________

**ተጨማሪ ሐሳብ፦** ይህን ታሪክ በዜና መልክ ለማቅረብ ሞክር። ስለተፈጸመው ሁኔታ የሚገልጽ ዘገባ አዘጋጅ፤ ከዋነ ኞቹ ባለታሪኮችና በቦታው ከነበሩ የዓይን ምሥክሮች ጋር የተደረጉ ቃል ምልልሶችን በዘገባው ውስጥ አካትት።



www.jw.org © 2012 Watch Tower Bible and Tract Society of Pennsylvania